የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሐምሌ 2 0 2015

ቁጥር/REF NO: 1/256/579/15

ለሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች

ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ቅበላን ይመለከታል፡፡</u>

እንደ ሀገር በየደረጃ ያለውን የትምህርት አሰጣጥን በማሻሻል የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ማስጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ይገኛሉ፡፡ የሚወሰዱ የጥራት ማሻሻያ እርምጃዎች በተወሰኑ የትምህርት እርከኖች ላይ ብቻ የሚወሰን ከሆነ የሚፈለገውን ሁለንተናዊ ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች ከቅድመ አንደኛ ደረጃ የአጠቃላይ ትምህርት እስከ ድህረ ምረቃ የከፍተኛ ትምህርት መሸፈን እንደሚገባው ይታመናል፡፡

በዚሁ አግባብ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች አከፋፈት ላይ ያለውን ክፍተት ለማረም በቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አቀባበል ላይ ተቀራራቢ ሥርዓት መከተል ያስፈልጋል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር በተደረገው ክትትልና ግምገማ ጥቂት በማይባሉ የመንግስትና የግል ተቋማት የድህረ ምረቃ ለመማር የሚያመለክቱ ተማሪዎች ምንም አይነት የመመዘኛና የመግቢያ ፈተና እንዳማይወስዱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ከ2016 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን እንደ ሀገር የመግቢያ ፈተናን (Graduate Admission Test) መስጠት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

**በመሆኑም፡-**

1ኛ/ በ2016 የድህረ ምረቃ ተማሪ የሚትቀበሉባቸውን ፕሮግራሞች ማለትም የመንግስት ተቋማት እስካሁን በቦርድ ፀድቀው በትምህርት ሚኒስቴር የተመዘገቡትን በመለየት እና የግል ተቋማት ከትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጣችሁን ፕሮግራም ዝርዝር እስከ ነሃሴ 20 ቀን 2015 እንድታሳውቁን፣

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ______

ቁጥር/REF NO: ______

2ኛ/ ሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተልኮና ትኩረት ልየታን መሰረት በማድረግ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ፈላጊዎች ማስታወቂያ በማውጣትና በመመዝገብ እጩ ተማሪዎቻቸውን እስከ መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም. እንዲያሳውቁ ፣

3ኛ.በተመሳሳይ ሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በባለሥልጣኑ በተፈቀደላቸው ፕሮግራሞች ላይ ብቻ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ፈላጊዎች ማስታወቂያ በማውጣትና በመመዝገብ እጩ ተማሪዎቻቸውን እስከ መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲያሳውቁ፣

4ኛ/ የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና (Graduate Admission Test) ለተቀራራቢና ተመሳሳይ ፕረግራሞች በጋራ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፈተና ማዕከል ከመስከረም 20 እስከ 28 2016 የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት የ2016 ትምህርት ዘመን የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ሥራዎች እቅድ ከዚህ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንድታዘጋጁ እያልኩ የጀመርነውን የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ በጋራ እንድናሳካ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

ለሚኒስትር ፅ/ቤት
ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈፃሚ
<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>
ለትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>
በዝርዝሩ ላሉት የቦርድ ሰብሳቢዎች
<u>አዲስ አበባ</u>